# በአዲስ አመት አዲስ ተስፋ እንሰንቅ: ተስፋችንንም እውን ለማድረግ ለተግባራዊ ስራ በአጭር እንታጠቅ፡፡

## ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ

መስከረም 2002 ዓ.ም

**ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ:**

አዲስ አመት ከዘመን ወደ ዘመን ፣ ከጭለማ ወደ ብርሃን፣ ከተስፋ እጦት ወደ አዲስ ተስፋ መሸጋገሪያ መድረክ ነው ። የአዲስ አመት መቃረብ፣ እንደ ህዝብ ያለፈው አመት እንዴት እንደነበረ፣ ምን ምን ሰው ሰራሽ ችግሮች እንደገጠሙን፣ የትኞቹ ተፈጥሮአዊና ከአቅም በላይ እንደነበሩ፣ የትኞቹን በብሄራዊ አቅማችን መመከት እንችል እንደነበር ወደኋላ መለስ ብለን የምንቃኝበት መልካም አጋጣሚ ነው። እንደ ግለሰብም አመቱን በደስታና በጥሩ ውጤት ካሳለፍን ባለፈው የምንደሰትበትና መጪውን አመት ደግሞ ከበፊቱም የተሻለ ለማድረግ፤ የበለጠ ለመደሰት እቅድ የምናወጣበት ይሆናል፡፡ ያሳለፍነው አመት የችግር፤ የመከራ፤ የሀዘን ከሆነ ደግሞ የችግሩን ምንጭ ፈልገን፤ መጪውም አመት እንደዚሁ የችግር እንዳይሆን፤ መፍትሄ አፈላልገን፤ ይህንን መፍትሄ ተግባራዊ የምናደርግበትን መንገድ አሰላስለን፤ ከወዳጆቻችን ጋር መክረን፤ ለተሻለ ህይወት፤ ለሰላማዊ ሕይወት ፤ በፍቅር ለተሞላ ሕይወት፡ ማድረግ ያለብንን ሁሉ ለማድረግ እንዘጋጃለን፡፡ ወደዚህ የሚያደርሰንን የግል ውሳኔም እንወስናለን፡፡ ውሳኔያችንን ተግባራዊ ለማድረግም በሙሉ አቅማችን ለመስራትና ለመንቀሳቀስ በፈጣሪያችን ፊት ለራሳችን ቃል እንገባለን፡፡

መንግስታት፣ ለሃገራቸው የነበራቸው ውጥን ምን ያህል እንደተሳካለቸው፣ ሳይሳኩ የቀሩት ደግሞ ምክንያታቸው ምን እንደነበር ግምገማ የሚያካሂዱበትና፣ ካለፈው ለመማር የሚያውጠነጥኑበት መድረክም ጭምር ነው አዲስ አመት። አንድ መንግስት ይህን ሊያደርግ እንዲቻለው ግን፣ በመጀመሪያ ከህዝብ ልብ የተቀዳ ሊሆን ይገባዋል። ዘወትር ህዝብን እንዴት እንደሚከፋፍሉና እንደሚያዳክሙ፤ እንዴት እንደሚዘርፉ፤ እንዴት እንደሚዋሹ እንዴት እንደሚያዋርዱና ቅስሙን እንደሚሰብሩ ሲያስቡ እንቅልፍ የሚያጡ የወያኔ ዐይነት አገዛዞች፣ አዲስ አመት በየአስራ ሶስት ወሩ ይዞላቸው የሚመጣውን ውስጣቸውን የመመርመር ዕድል ለራሳቸው የነፈጉ የመንፈስ ድሆች ናቸው ማለት ማጋነን አይመስለኝም። የአንድ አገርና ሕዝብ ማንነት ግን በጊዜው ባለው መንግስት ምንነት አይለካም፡፡ አገርና ሕዝብ ከመንግስት በላይ ነው፡፡ እስከአሁን አልሳካ ብሎን ነው እንጂ መንግስትማ ሌላ ነገር ሳይሆን በሕዝብ የተወከለ የሕዝብ አገልጋይ መሆን ነበረበት፡፡ የሕዝብ አገልጋይ መንግስት በሚኖር ጊዜ ደግሞ ከላይ ያልኩትን አይነት የራሱንና የአገሩን ሂደት በእውነት ላይ ተመስርቶ ገምግሞ ለመጪው አመት ምን ለማድረግ እንደሚያስብ ማህበረሰቡን አማክሮ፤ ወደፊት እንዴት እንደምንሄድ ሁላችንም እንኳዋን ባይቻል አብዛኞቻችን የተስማማንበት አቅጣጫ ተቀይሶ ያንን ተግባራዊ ለማድረግ ሁላችንንም በውዴታ ሸሚዛችንን ጠቅልለን ለመስራት እንድንነሳ ባንቀሳቀሰን ነበር፡፡ ይህ ግን አልሆነም፡፡ በሁሉም አቅጣጫ አገሪቱን ወደሁዋላ እየጎተተ ካለ ዘረኛ ስርአት ይህን መጠበቅ ትተናል፡፡ ከዛሬ ነገ ይሻሻላሉ፤ ልቦና ይገዛሉ፤ ከርሳቸውን ከሞሉ በሁዋላ ከራሳቸውና ከጠባብ ቡድናቸው በላይ ለአገር ማሰብ ይጀምሩ ይሆናል፤ ሌላ ቢቀር ለራሳቸው ታሪክና ለልጆቻቸው ብለው ቀና ነገር ማሰብ ይጀምራሉ ብለን በትእግስት ጠበቅናቸው፡፡ እየተሻሻሉ ሳይሆን እየባሰባቸው ነው የሚሄደው፡፡ ስለዚህ ያለፈውን አመት የግል ህይወታችንን መዝነን ስለወደፊቱ ኑሮአችን አቅደን ተግባራዊ ለማድረግ የምንንቀሳቀሰውን ያክል ያሳለፍነውን አመት እንደህዝብ፤ እንደ አገር፤ የመገምገም፤ ከዚያም የወደፊት አቅጣጫችንን የመቀየስ፤ የቀየስነውንም እቅድ በተግባራዊ እንቅስቃሴ የመተርጎሙ ስራ በኛ በአገሪቱ ህዝብና በዜጎቿዋ ላይ የተጣለ የትውልድ እዳ ሆኖአል፡፡

- **ታዲያ ያለፈውን አመት እንደ አገርና እንደ ህዝብ እንዴት አሳለፍነው?**

ከቀድሞው አመት በተሻለ ሕዝባችን ጠግቦ በላ? ልጆቹን የተሻለ መገበ? ገበሬው ከችጋር ተላቀቀ? ከተሜው ሰርቶ አደር አለፈለት? የመንግስት ሰራተኛው ተመቸው? ነጋዴው የተሻለ አተረፈ፤ ንግዱ ተሙዋሙዋቀ? ባጠቃላይ ኑሮ ካለፈው አመት የተሻለ ነበር? ካልሆነስ የኢኮኖሚ ችግሩ ሁላችንንም እንደዜጎች በእኩልነት አጠቃን? የሀብት ክፍፍሉስ ከቀድሞው በተሻለ የተመጣጠነ ነበርን?

ኑሮአችን የበለጠ ዘምኖአል፤ ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጋር በመላመድ የወደፊቱ ሕይወታችንን ከሌላው አለም ጋር ወደሚቀራረብበት አቅጣጫ እየመራነው ነው? ልጆቻችን በሚያገኙት የትምህርት ጥራት የተነሳ ከተቀረው አለም ልጆች ጋር በእውቀት እየተቀራረቡ ነው?

የአዲሱን ሺኛ የመጀመሪያ አመት ስናገባድድና አዲሱን ስንቀበል በተሻለ መብታችን ተከበረ? የተሻለ ነፃነት ተሰማን? የተሻለ የዜግነት ስሜት፤ የእኩልነት ስሜት ተሰማን? ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ተጠጋን? የተሻለ ዳኝነት አገኘን?

አሁን ከቀድሞው የተሻለ ደህንነትና ሰላም ይሰማናል? አገራችን ከጦርነት ተላቃለች?

ማህበረሰባችን ውስጡ ጤነኛ ነው? በአገራችን ፍቅር ሰፍኖአል? ሀይማኖቶቻችን የሰላምና የፍቅር ቤት ናቸው? ማህበረሰባችን ውስጥ የይቅርታ ስሜት ሰፍኖአል?

ለመሆኑ ስለወደፊቱ የአገራችን ሁኔታ ጥሩ ስሜት ይሰማናል፤ ጥሩ አቅጣጫ ይታየናል?

እነኝህንና መሰል ጥያቄዎችን በምንመልስበት ሁኔታ ነው ያለፈው አመት ኑሮአችን ብቻ ሳይሆን የመጪው አመት አቅጣጫችን የሚገለፀው።

**ውድ የአገሬ ሰዎች፡**

ከላይ ያነሳሁዋቸውን ጥያቄዎች ሁሉ በአወንታዊ መልክ ብመልሰው እጅግ ደስተኛ በሆንኩ ነበር። ወያኔ/ኢሕአዴግ እስከሚያመን ድረስ እንደሚነግረን ሁሉ እውነትም ማህበረሰባችን ጥጋብ በጥጋብ ቢሆን፤ ገበሬው ሚሊዮን ቢቆጥር፤ ነጋዴው ንግዱ ቢስፋፋ፤ የመንግስት ሰራተኛው ከምግቡ አልፎ ስለሌሎቹ ፍላጎቶቹ ማሰብ ቢችል፤ ዳኞች ለእውነት ቢፈርዱ፤ ፖሊስ በሀሰት ሰው ባያስርና ባያሰቃይ ወይንም በውሸት ሰላማዊ ሰውን ወንጀለኛ ነው ብላችሁ መስክሩ ብሎ እስረኞችን ባይቀጠቅጥ፤ ማህበረሰባችን ያለፍርሀት በሙሉ ልቡ መኖር ቢችል፤ ቂምና ጥላቻ ጠፍቶ ፍቅር ቢሰፋፋ፤ የሕዝባችን የይቅር ባይነትና የአብሮ መኖር ስሜቱ ቢደነድን፤ የሀይማኖት አባቶቻችን የተከበሩ ቢሆኑ፤ ማን ደስ አይለውም? እንደነመለስ ውስጡን ጥላቻና ቂም እንደነቀርሳ የሚበላው የመንፈስ በሽተኛ ካልሆነ በቀር አገር ቢሻሻል፤ ሕዝብ ቢመቸው የሚጠላ ጤነኛ ሰው አለ ብዬ አላምንም።

የቸገረንና ሁኔታውን እጅግ አሳሳቢ የሚያደርገው ከሞላ ጎደል በሁሉም አቅጣጫ፤ ማለትም በኢኮኖሚው፤ በፖለቲካውና በማህበራዊው ዘርፍ ካለፈው የተሻልንበት ሁኔታ አለመፈጠሩ ብቻ ሳይሆን ነገሮች በአደገኛ ሁኔታ እያደር ይበልጥ እየተበላሹ መሄዳቸው ነው። ሁኔታዎች በዚህ ከቀጠሉ በማህበረሰባችን ላይ የሚመጣው ጣጣ ማለቂያ የሌለው መሆኑ፤ እነመለስ ካደረሱን የገደል ጫፍ ላይ ተረባርበንና ተያይዘን መመለስ ካልቻልን ገደሉ ውስጥ ገብተን ከተከሰከስን በሁዋላ መመለሻ ስለሌለው ነው ይህንን ችግር ለአንዴና ለሁሌ ለመንቀል በፍፁም የአስቸኩዋይነት ስሜት ታጥቀን መነሳት ያለብን።

**ውድ ወገኖቼ!**

መቼም ያላችሁበትን የኑሮ ሁኔታ እኔ ብነግራችሁ ለቀባሪው ማርዳት ነው የሚሆንብኝ። ግን ያለንበትን አደገኛ ሁኔታ ለማስረገጥና ማስታወሳችሁን ለመቆርቆር ያክል ብቻ በዚህ ባሳለፍነው አመት ከተፈፀሙ በርካታ ኩነቶች አንዳንዶቹን ለአብነት ያክል ልጠቃቅስ፡

በግብርናው ምርት ማደግና በገበሬው ሀብታምነት ላይ የተመሰረተ ነው የተባለለት የኢኮኖሚ እድገት እያደር እየጨመረ በሄደው የገበሬ ረሀብተኛ ብዛት የወያኔን ውሸት ሊያምኑለት ለሚፈልጉት ፈረንጆች እንኩዋን የማይዋጥ ሆኖአል። በቅርቡ የእንግሊዝ መንግስት ባስጠናው ጥናት ለግብርና ምርት እድገት ምክንያቶች ናቸው የተባሉት የመሬት አቅርቦትና የምርታማነት በእጥፍ መጨመር በፍፁም ሊታመን የማይችልና ምናልባትም በወያኔ የተፈበረከ አሀዝ ሊሆን እንደሚችል ሲፈራ ሲቸር አጋልጦአል። ለነገሩ ፈረንጆቹን ያታልልበት እንደሆነ እንጂ ቀድሞውኑም

የኢትዮጵያ ገበሬ የሚባለው እድገት እንደሌለ ከኑሮው ያውቀዋል፡፡ በቅርቡ የአርጀንቲና ማእከላዊ እስታትስቲክስ ፅ/ቤት ሰራተኞች በመንግስት ግፊት የሚፈበርኩት የውሸት አህዝ ህሊናቸውን አቃጥሎት በምሬት “ውሸት በቃ፤ ህዝብ ማታለል በቃ፤ እኛንም በማስዋሸት ከፈጣሪያችን ጋር አታጣሉን” ብለው ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት የአርጀንቲናን መንግስት እንዳዋረዱት፤ የኛዎቹም የእስታትስቲክስ ፅ/ቤት ሰራተኞች ከፍርሀት ሰንኮፋቸው ወጥተው ይህን ማድረግ ባይችሉም፤ የእንግሊዞቹ ጥናት የነመለስ ውሸት ለ”ቱሪስቶቹም” የማይዋጥበት ደረጃ ላይ መድረሱን አሳየን፡፡

በውጭ ምንዛሪ እጥረት፤ በብድር ገንዘብ መጥፋት፤ በከተሞች በተንሰራፋው አስከፊ ድህነት ምክንያት ገበያተኛ በመጥፋቱ፤ በመብራት መቋዋረጥ፤ በውሀ እጥረት፤ ሆን ተብሎ በተፈጠረ የዋጋ ንረት፤ ባለሀብቱን ከጨዋታው ለማስወጣት አገዛዙ በሚያስቀምጠው መረን የለቀቀ የዝርፊያ ታክስና: በአለም ላይ የተከሰተው የኢኮኖሚ ቀውስ ተደማምረው የከተማው ኢኮኖሚ ከሞላ ጎደል ባለበት መቆሙን፤ የአገራችን ነጋዴዎች በድፍረት የሚናገሩበት፤ ፈረንጆቹም በየጋዜጦቻቸው በግልፅ የሚፅፉበት ደረጃ ላይ ተደርሶአል፡፡ የዋጋ ግሽበቱ ለከተማው ነዋሪ ብቻ ሳይሆን 53 ከመቶ ለሚሆነው በከፊል ሽምቶ ለሚበላው አርሶ አደር ኑሮን እሬት እንዳደረገበት የሚታወቅ ነው፡፡ በቅርቡ የቢቢሲ ፊልም አንሺዎች አክሎግ አንዳርጌ የሚባል ገበሬን ህይወት ተከታትለው ለአለም ያሳዩት የስቃይ ህይወት የዛሬውን የአገራችንን ገበሬ ህይወት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ በለንደን የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ የዚህን ፊልም መታየት አጥብቆ ሲኮንነው በምክንያትነት የጠቀሰው፤ የመንግስትችንን ‹የልማት መንግስትነት› ምስል አጥፍቶአል፤ በአገራችን ጥቂት ቦታዎች ችግር ቢኖርም ጠቅላላው በአገሪቱ በቂ ምርት እናመርታለን፤ ጥጋብ በምድራችን ሰፍኖአል እያለ ነበር፡፡ አለቃው መለስም በአገሪቱ ስላለው ችጋር ሲጠየቅ ጠረጴዛ እየመታ ለፓርላማው 70 ሚሊዮኑ የኢትዮጵያ ገበሬ አልፎለታል፤ ተመችቶታል እያለ በድፍረት ይደነፋ የለ!
ነገሩ ያልተነካ ግልግል ያውቃል የሚሉት አይነት ነው፡፡ የሱ ህይወት እንደዚያ ገበሬ የተጎሳቆለ ስላልሆነ የሱን ኢትዮጵያ ምስል እንዳያበላሽበት ብሎ ነው፡፡

ምን ያድርግ! ከሱ ጠባብ ምህዳር አንፃር ካየነው እውነቱን እኮ ነው! በርግጥ ኢኮኖሚው የቆመውና የቀነሰው በዚህም የተጎዳው ብዙሀኑ ኢትዮጵያዊ ነው እንጂ ጥቂቶቹ ባለጊዜዎች ምን ጎድሎባቸው! ይህ የኢኮኖሚ ችግር ሆን ብሎ የፈጠራቸውና ያደለባቸው አዳዲስ ባለሀብቶች ሞልተዋል፡፡ በልዩ ኢንቬስተር ፈቃድ በአስርሺዎች የሚቆጠር ኩንታል ሲሚንቶ ከፋብሪካው በርካሽ እንዲገዙ ተፈቅዶላቸው ይህንን ሲሚንቶ በመከላከያ መኪና ጭነው ሲሚንቶ ተራ ከእጥፍ በላይ ዋጋ ለቸርቻሪ ነጋዴ አራግፈው በአንድ ጀምበር ሚሊየነር የሆኑ የቀድሞ ታጋዮች የኢኮኖሚ ችግሩ እንዴት ይሰማቸው? ከሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ መሬት በነፃ ተሰጥቶአቸው በመከላከያ ንብረት ህንፃ አሰርተው በአስር ሺዎች እያከራዩ የሚዝናኑ የዘመኑ ባለሙዋሎች እንዴት የሰዉ መደሕየት ይሰማቸው! ወይንም ደግሞ ነጋዴው ላይ ሆን ተብሎ በውሸት የተጫነውን ታክስ ከባለስልጣናት ጋር ተነጋግሬ አስቀንስልሀለሁ በሚል በአንድ ጊዜ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ብር ግቦ የሚቀበሉት አቀባባይ የጊዜው “ተቀናሽ ወታደር” ባለሀብቶች ሕዝቡ የሚያወራው የኢኮኖሚ ችግር “የቀናተኛ ወሬ” ቢመስላቸው አይገርምም! እንደ ስብሀት ነጋና አዜብ መስፍን በትግራይ ህዝብ ስም በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ማካበታቸውን፤ የአገሪቱ ዋና ባለሀብት መሆናቸውን በድፍረት በሬድዮ ይናገሩት የለም እንዴ! በዚሁ በትግራይ ህዝብ ስም የፈለጉትን ያህል ብር ከባንክ ለመውሰድ የሚችሉና ለባንክ ምንም ብድር ሳይመልሱ ሀብት አካብተው ገሚሱን ሀብት በዶላር ወደ ውጭ አገራት የሚያሸሹ የፖለቲካ ሙሰኞች፤ አለያም ከነሱ ጋር ተጣብቀውና ተመሳጥረው ሕዝቡን የሚዘርፉ ጥቂት ወራዶች ሼራተን ቁጭ ብለው ቀድሞ ስሙን በስርአት እንኳዋን የማይጠሩትን ባለቀለም ውስኪ እየጠጡ የህዝቡን ምሬት “በትግራይ ህዝብ ብልፅግና የመቅናት” አድርገን እንድንወስደው ሊያሳምኑን ቢሞክሩ አላማቸው ይረዳናል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ እነኝህን አዳዲስ የሸፍታ ባለሀብቶች ጠንቅቆ ያውቃቸዋል፡፡ ዘርፈው ብር ያካበቱትን ላባቸውን አንጠፍጥፈው ገንዘብ ከሰሩት ይለያቸዋል፡፡ ዘራፊዎቹ ያለምንም ስጋት ዘርፈው ላገኙት ገንዘብ ምንም ክብር የሌላቸው መሆኑንና ይህንንው የተሰረቀ ብር በየመሸታ ቤቱ ሲበትኑትና ያልለመዱት መጠጥ ሲያቀረሻቸውና ሌላውን ህዝብ ለምን አየኸኝ ብለው ሲገላምጡ ያውቃቸዋል፡፡ እነኝህ አዳዲሶቹ ባለሀብቶች በዘረፋ ያገኙትን ሃብት እንደቀጤማ በየደረሱበት የሚነሰንሱት፣ ቀኑ የእኛ የትግራይ ሰዎች ነው በሚል ዘረኛ ብልግና ታጅለው ነው፡፡

አላማቸው እንደተቀረው የሃገሪቱ ህዘብ በድህነት የሚማቅቀውን የትግራይ ህዝብ እንደነሱ በዘረፋ ተጣቃሚ ተደርጎ በሌላው ወገኑ እንዲጠላ በእዚህም የህዝበ መጠለላት የትግራይ ሀዝብ የዘረኛ ስልጣነቸውና ሃብታቸው መንጠልጠያ ለማድረግ ነው ። ይህንን የጥቂት ዘረኞች መርዘኛ ሴራ የትግራይ ህዘብ ከሌሎቹ ኢትዮጵያዊ ወገኖቹ ጎን በመቆም በጋራ ያከሽፈዋል እንጂ ጥቂት ዘረኞች ባጠመዱለት አደገኛ ወጥመድ እንደማይወድቅ ትስፋ አለን፡፡

ባለፈው አመት ከተፈጠሩት ክስተቶች መሀል ለሚገጥሙትና እራሱ ለፈጠራቸው የኢኮኖሚ ችግሮች የአገርን ጥቅም በማስቀደም መፍትሄ መፈለግ የማይሆንለት ይህ ጠባብ ዘረኛ ቡድን፤ የስልጣን እድሜው ከማለቁ በፊት የአገሪቱን ሀብት በቶሎ ለመቀራመት ሲል፤ ለአገሪቱ ዘላቂ መርዝ ጥሎ የሚያልፈውን አገሪቱን በኦፊሴልና በኢንቬስትመንት ስም ሸንሽኖ መሸጥን እንደ ትልቁና አዲስ ግኝት አድርጎ ይዞታል፡፡ ከየት እንደሚያመጣው ገና ያልታወቀውንና መሬቱ እንኩዋን ቢኖር ምን አይነት ዘላቂ አካባቢያዊ የብዙሃ ሕይወት ችግር እንደሚያስከትል ሳያሰላ፤ መሬት ለአዲሶቹ የእስያና የመካከለኛ ምስራቅ ወዳጆቹ መቸብቸብ ፈለገ፡፡ ይታያችሁ ይህ አገዛዝ በመሬት ጥበት የሚሰቃዩ ኢትዮጵያውያን በመጠኑ መሬት ወደሚገኝበት ሌላ የአገሪቱ ክፍል ሄደው እንዳያርሱ በክልል ኬላ አቁዋቁም አጥብቆ የሚከለክል አገዛዝ ነው፡፡ መሬት አጥቶ የሚሰቃየው የከምባታ ገበሬ መሬት በስፋት ካለበት የአፋር ወንድሙ ኩርማን መሬት ገዝቶ እንኩዋን አርሶ ከሚጠቀም ለሕንድ ባለሀብት በሚሊዮን ሄክታር የሚቆጠር መሬት መሸጥ ይቀለዋል፡፡ የአገሬው ሕዝብ እንኩዋን ቢያርሰው፤ ቢያንስ ምርቱ ለአገሪቱ ህዝብ የሚቀር ነበር፡፡ እነሱ ግን አገር አይታያቸውም፡፡ የሚታያቸው ዘርና ጎጥ ብቻ ነው፡፡ ይህ ለሚገዛው ህዝብ ጥላቻ ብቻ ያለው አገዛዝ የሚሸጠው መሬት ምርታቸውን አገራቸው ወስደው ለሕዝባቸው ለመሸጥ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ነው፡፡ እነኝህ ሀፍረት የሚባል ነገር ያልፈጠረባቸው ሰዎች ይባስ ብለው ይህ እርምጃ የአገራችንን የምግብ ደህንነት ያረጋግጣል ብለው ሊሳለቁብን ይሞክራሉ፡፡ አይናቸውን በጨው አጥበው እራሱን መመገብ ያቃተውን በአገዛዛቸው ስር የሚሰቃይ ዘንድሮ ከ12 ሚሊዮን በላይ የደረሰ ገበሬ ለምን በደንብ አትመግቡልንም ብለው ለጋሾቻቸውን ይዘልፋሉ፡፡ ተዋርደው አገር ያዋርዳሉ፡፡

**ውድ ያገሬ ሰዎች!**

የኢትዮጵያ ህዝብ የዘንድሮውን አዲስ አመት የሚያከብረው በጭለማ ተውጦ መሆኑን እናውቃለን። ጭለማ ስንልም የኤሌክትሪክ ብርሃን እጦትም ብቻ ሳይሆን፣ የአዲስ ተስፋ እጦትም እየተፈታተነው መሆኑም ግልፅ ነው። በግንቦት 97 ምርጫ በህዝብ ድምፅ የተረታው ወያኔ፣ ራሱን በስልጣን ለማቆየት በወሰዳቸው መጠነ ሰፊ የእመቃና የአፈና ተግባራት፣ ለመከላከያ ሃይሉ፣ ለሰላዮቹ፣ ለጠባብ ብሄርተኛ የፈሪ ስትራተጂው፣ ለሙስናውና ለገንዘብ ማሸሹ ተግባራት ለማውጣት የተገደደው ወጪ ከሃገሪቷ አቅም በላይ መሆኑ አንዱ ምክንያት ነው ።

አዎን ወያኔ በግንቦት 97 የደረሰበትን ሽንፈት ለማድበስበስና፣ በሃገር ብሄርተኝነት ስም የህዝብን ድጋፍ የሚያገኝ መስሎትም ሆነ፣ ከቡሽ አስተዳደር የገንዘብ ድጎማ አገኛለሁ በሚል ስሌት፣ ሰራዊቱን ሶማልያ ውስጥ በማስገባት በህዝቡ ላይ ከፍተኛ ወንጀል ከመፈፀሙም ባሻገር፣ የድሃ ሃገራችንን ሀብት አላስፈላጊ የሆነ ጦርነት ላይ በማባከን ለሃገር ዕድገት ሊውል ይችል የነበረውን ብሄራዊ ሃብት በጦርነት ላይ አውድሞ፣ በሺህ የሚቆጠሩ የሠራዊቱ አባላት እንዲሞቱና አካለ ጎዶሎ እንዲሆኑ ካደረገ በሁዋላ በዚሁ ባሳለፍነው አመት ጭራውን ቆልምሞ ወጥቶአል። እጅግ የሚዘገንነው፤ የወገኖቻችን አስከሬን በየመንገዱ ሲጎተት እያየን ልባችን ሲደማ፡ እረ ያለቁብንን ልጆቻችንንና ወንድሞቻችንን ብዛት እንኳዋን ንገረን፤ አንዴ እንኩዋን እናልቅስላቸው ተብሎ ቢለመን ‹ማን እንደሞተ ለህዝቡ መናገር አያስፈልግም፤ ለናንተ ለህዝብ ተወካይ ተብዬዎች ምንም አይጠቅማችሁም፤ እኔ ካወቅሁ ይበቃል› ብሎ የሚያፌዝ ጋጠ-ወጥ፤ እንዲህ በትእቢት የሚወጠረው በዚሁ እንደ አልባሌ ነገር ደሙ በየቦታው በሚፈሰው ወታደር ተማምኖ መሆኑን ስናስብ፤ በእውነት ይዘገንናል፡፡ ዛሬ ስለመፃኢው አዲስ አመት ስናሰላስል፣ ምን ብናደርግ ነው ራሱን በስልጣን ለማቆየት ሲል፣ የጎረቤት ሃገራትን የመውረር ወንጀል የማይፈፅም፤ የፖለቲካ መብታችን ይከበር የሚሉ የአገሩ ተቃዋሚዎችን ለመከላከል ሲል የአገሩን የድንበር መሬት ለሌሎች አገሮች የማያስረክብ፤ በምትኩ ግን የሕዝብ ደህንነት ለማስጠበቅ በሕዘቡ የታክስ ገንዘብ የሚንቀሳቀሱትን የአገሪቱን የመከላከያ ሰራዊት የአገሪቱን ድንበር

ለመጠበቅ ብቻ የሚጠቀም መንግስት መመስረት የምንችለው ብለን የምናሰላስልበት መልካም አጋጣሚ ነው እላለሁ ።

ወያኔ ለጠባብ ዘረኛ የፈሪ ስትራተጂው ሲል የሚያደርጋቸው ተግባሮችም፣ የህዝባችንን ህይወት ከጨለማ ወደበለጠ ድቅድቅ ጨለማ እንዲያሽቆለቁል ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ነው። በመሃል ሃገር በእብሪት የያዘው የአናሳ ስልጣን የማከተሙ ተፈጥሮአዊ ህግ አይቀሬ መሆኑን በምርጫ 97 በተከናነበው ውርደት ስለተረዳ እሱ በስልጣን እስካለ ድረስ ምንም አይነት የሰለጠነ ፖለቲካ በአገሪቱ ሊካሄድ እንደማይችል በግልፅ፤ ፅፎ ባፀደቃቸው ሕጎችና ዝለሉ ሲላቸው በስንት ከፍታ እንጣጥ እንበል በሚሉ ወራዳ ዳኞች በሞላው ፍ/ቤቱ አሳይቶናል በዚሁ ባሳለፍነው አመት፡፡ ትንሽም ቢሆን ለመተንፈስ ማህበረሰቡ ይጠቀምባቸው የነበሩትን የግል ሚዲያዎች እውነት መናገር ወንጀል በሚያደርግ የሚዲያ ሕግ በመጀመሪያ አሰራቸው፡፡ ቀጠለና ምናልባት እንደ ምርጫ 97ቱ ጊዜ ትንሽ የነፃነት ስሜት ተሰምቶአቸው ስለዴሞክራሲ፤ ስለመብት፤ ስለዜግነት እንዳያስተምሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እግር ተወርች የሚያስር፤ በፈለገው ጊዜ ያለምንም ምክንያት ሊዘጋቸው የሚያስችለው ሕግ ብጤ አወጣላቸው፡፡ ሕጉን ለማመን የቸገራቸው ፈረንጆች ምናልባት ቀዳዳ እንዳለ ብለው እንዳያስቡ ወዲያውኑ 42ቱን መያዶች ከደቡብ ክልል በማገድ ፍላጎቱ ምን እንደሆነ በግልፅ አስቀመጠ፡፡ ጉዳዩ አሳዛኝ ባይሆን ኖሮ አስቂኙ ነገር ለመታገዳቸው ከቀረበው ምክንያት አንዱ የመንግስትን የግብርና ፖሊሲ አይደግፉም የሚል ነው፡፡ ‹ኬሚካል ማዳበሪያ ለአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች ላይጠቅም ይችላል› ብሎ ማመን ድርጅት የሚያዘጋበት፤ መለስ የሚያምነውን የፖሊሲ መስመር አለማመን በአምክህኖታዊ ውይይት የሚፈታ የመከራከሪያ ነጥብ መሆኑ ቀርቶ በፀረ ሕዝብነት፤ በጥገኝነት፤ በሌላም ወንጀሎች የሚያስጠይቅበት ጉደኛ ጊዜ ላይ ደረሰናል፡፡ በዚህ ከቀጠለ የመለስ የቁም ሀውልት ተሰርቶ፤ በበረከት መፈክር አውጪነት፤ ‹ከጀግናው፤ ከአዋቂው፤ ከብልሁ፤ ከጂኒየሱ፤ ከአለም አንደኛው፤ መሪያችን ጋር ወደፊት› እያለ ሕዝቡ እንዲጮህ የሚገደድበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም፡፡ ከዚያም የመሪነት ችሎታ በደም የሚተላለፍ ነው ብሎ ሚስቱን ወይንም ልጁን የሚተካበት የሰሜን ኮሪያው አይነት የጨለማ ዘመን ውስጥ መግባት አጭር እርምጃ ነው፡፡ ጅማሬውም እየታየ ነው፡፡ በመጨረሻም ምናልባት በነኝህ ሕጎች የተረሳ ነገር ካለ በሚል አዲስና ሁሉን አቀፍ የፀረ-ሽብርተኛ አዋጅ ታወጀለት፡፡ ይህኛው አዋጅ ደግሞ ማንንም ሰው (የአይኑ ቀለም ያላማረውንም) ሽብርተኛ ብሎ የመጥራትን፤ ከዚያም ላልተወሰነ ጊዜ ከማንም ጋር እንዳይገናኝ ማሰርን፤ በሰቆቃ መጥበስን፤ ንብረቱን መዝረፍን የሚፈቅድለት ህግ አወጣ፡፡ በዚህኛው ጉደኛ ህግ ደግሞ እሱ አሸባሪ ያለውን ሰው በስልክ ማውራትም ሆነ ምናልባትም ስሙን መጥራት በራሱ የሽብርተኛ ተባባሪ አሰኝቶ ያሳስራል ወይም ንብረት ያዘርፋል፡፡ በአፓርታይድ ጊዜ ነጮቹ በጣም በሚንቁዋቸው ጥቁሮችና በነፃነት ተዋጊዎቹ ላይ እንኳዋን እንደዚህ አይነት ሕግ አላወጡም፡፡ ይታያችሁ!!! ወያኔ እንዲህ አይነት ነውረኛ ተግባራት ከዚህ በፊት ሳያደርግ ቀርቶ አይደለም፡፡ ሕጉ ሳይኖርም እሱ ሲያደርጋቸው ነበር፡፡ የአሁኑን ሕግ የሚለየው አንድም በግልፅ ሕብረተሰቡን ለመዝረፍ የተነሳ መሆኑን፤ ፖለቲካውን ለመቆጣጠር ኢኮኖሚውን መቆጣጠር አለብኝ የሚለው የቆየ እምነቱን እሱ የማይወዳቸውን ባለሀብቶች በመዝረፍ፤ እሱ የሚወዳቸውን ሀብታሞች ለመፍጠር ያለመ መሆኑ ነው፡፡ ሌላው ይህ ሕግ የሚያሳየው ግን የትእቢቱን ለከት ማጣት ነው፡፡ እንደዚህ አይነቱን የሰብአዊ መብት ጥሰትና የመንገድ ላይ ማጅራት መቺነት ፊት ለፊትና በሕግ ከለላ አደርገዋለሁ ብሎ ማሰቡ፤ ይህንንም ሕዝቡ ፀጥ ረጭ ብሎ ይቀበለኛል ብሎ ማመኑ ነው፡፡ የኢትዮጵያውያንን ወኔ አሸንቼ ጨርሼዋለሁ ብሎ መመካቱ ነው፡፡

**ውድ ያገሬ ሰዎች!**

በመገባደድ ላይ ያለው አመት ብዙ የሙስና ተግባራትም የተጋለጡበት አመት ነበር ። በዝምድና አምቻ ጋብቻ የተሳሰረው የወያኔ ጠባብ ብሄርተኞች ቡድን እንዴት አድርጎ የመከላከያ ሃይሉን መካከለኛና ከፍተኛ አመራር በጥቅም በተሳሰሩ ጥቂት ዘረኞች እንደሞላውና፣ እነዚሁም የጦር መኮንኖች መሬት በመቀራመትና፣ የባንክ ብድር ያለመያዣ በመውሰድ እንዴት በሚሊዮኖች የሚያወጡ ቪላዎች ባለቤት ሊሆኑ እንደቻሉ ድርጅታችን ግንቦት7 ያጋለጠበት ጊዜ ነበር፡፡ ይህን የሚያውቁ የቀድሞ ታጋዮች በተለይም የብአዴን አባላት ይህንን አይን ያወጣ ዘረኛነት በመቃወም በግላጭ ኮንነውታል፡፡ ከዚያም አልፎ በሰራዊቱ ውስጥ ከፍተኛ ተቃውሞ ቀስቅሶበታል፡፡ የስርአቱን ኢፍትሃዊነት የኮነኑ የአማራ መኮንኖችን፡ ለማስመሰል ደግሞ የግንቦት7 አመራር አባላት ዘመዶችን ጨምሮ መንግስቴን

ሊገለብጡብኝ ሲሉ ያዝኩዋቸው ብሎ እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ በደርግ ጊዜ ይደረግ እንደነበረው ወፌ ኢላላ የተገረፉበት፤ ብልታቸው ውሀ በሞላው ጠርሙስ የተወጠረበት፤ ጥፍራቸው በጉጠት የተነቀለበት፤ የወያኔን ስርአት ዘረኛነት ብቻ ሳይሆን ጨካኝነትና ሞራል አልባነት ፍንትው አድርጎ የታየበት፤ የወያኔ የጦጣዎች ፍርድቤትም ማስመሰል የሚባለውን ነገር ሁሉ እርግፍ አድርጎ ትቶ፤ ዋናዎቹን ተከሳሽ ያላቸውን ማስረጃችሁን አቅርቡና ተከራከሩ፤ በቦታው የሌሉትንና በተባባሪነት የተከሰሱትን ጥፋተኛ ብሎ ለመፈረጅ ምንም የማይሰቀጥጠው እቃ መሆኑን ያሳየበት ጊዜም ነበር ይህ ያሳለፍነው አመት፡፡ በዚህ ፍ/ቤትና በሁዋላም በፍትህ ሚኒስቴር ተብየው በአሰፋ ከሲቶ ላይ የወሰደው እርምጃ፡ የወያኔ አይነት ዘረኛ ስርአት የሚጠላውን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የሚያገለግሉትን ተቋማትና በስሩ የሚሰሩትን አሽከሮቹንም ለማዋረድ ምንም አይኑን የማያሽ፤ ክብር የሚባል ነገር የማያውቅ መሆኑን ያስረገጠበት ጊዜ ነበር፡፡

የነመለስ አይነት በጥላቻ የተሞላ ዘረኛ ስርአት የሚገዛውን ማህበረሰብ ሙብት በመርገጥና በማዋረድ ብቻ አይደለም የጥላቻ ቂሙን የሚወጣው፡፡ የዚያን ማህበረሰብ የሞራል እሴቶችንም በመግደል እንጂ፡፡ ያ  ማህበረሰብ ምንም የሚመካበትና አለኝ የሚለው ቁሳዊ፤ ተቁዋማዊም ሆነ ስነልቦናዊ እሴቶች እንደሌሉትና እንዳይኖሩት በማድረግ እንጂ! ለዚህ ነው ማህበረሰቡ የሚመካባቸውንና የሚሳሳላቸውን ተቁዋማት አንድ በአንድ የሚደረምሳቸው፡፡ የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር የሆነችውን ብርቱካን ሚደቅሳን ለምን እውነት ታናገርሽ፤ ለምን እንደኛ ውሽታም አልሆንሽም ብሎ ባሳለፍነው አመት በግፍ በድጋሚ ሲያስር፤ ማህበረሰቡ የሚያምንበትን የሽምግልና ተቋዋም ገድሎ፤ የሽማግሌ ተብዬዎችን ስብእና አዋርዶ፤ ሽምግልና ማለት ለእውነት፤ ለፍትህ፤ ለእርቅ የቆመ ባህላዊ ሸንጎ ሳይሆን፤ ምንም መርህ የሌላቸው በአብዛኛው ለሆዳቸውና ለጥቅማቸው የቆሙ ጥቂት እድሜያቸው የገፋ ሰዎች ስብስብ አስመስሎ፤ እነሱንም የግፉ አካል አድርጎ ነው፡፡ ማህበረሰቡ በፅኑ የሚያምንባቸውን ከዚህ ጊዜያዊ አለም ይልቅ ለማያልፈው ዘላለማዊ ሕይወት ቆመናል የሚሉ የሀይማኖት ተቋዋማትንና የሀይማኖት አባቶችን፤ ከማንም ተራ ሰው ያልተሻሉ፤ ለስጋቸው ያደሩ፤ የነዋይ ፍቅር ያሰከራቸው ሰዎች እስከሚመስሉ ድረስ እርስ በእርሳቸው ያባላቸዋል፡፡ ከዚያም አልፎ ባደባባይ በተራ ዱርዬዎች ጳጳሳት ሲደበደቡና በራቸው ሲሰበር ህዝቡ እያየና እየሰማ፤ እግዚአ የሚባልበት ቦታ እንኩዋን እንደሌለ እንዲያምን፤ ሞራሉ ጭራሹኑ እንዲላሽቅ ያደርገዋል፡፡ ይህ አልበቃ ብሎት አብረውና ተከባብረው የኖሩ ሀይማኖቶች እንዲጋጩ፤ በደሴ ላይ እንዳደረገው አንደኛው ሀይማኖት የአንደኛው ምቀኛ፤ ለአንዱ የተባለውን መሬት ሌላው ተቃውሞ እንዳስከለከለ አድርጎ በቡችሎቹ በማስወራት፡ አልጋጭ ሲሉለት የሚያጣላበት ሌላ ዘዴ ሲያሰላስል ያድራል፡፡

የወያኔ አይን አውጣነት በፍፁም ለከት ያለው አይደለም፡፡ ይህን ሁሉ በደል እየፈፀመም ህብረተሰቡ "ከዚህም የባሰ ሊመጣብኝ ይችላል" ብሎ እንዲያስብ መሀሪ፤ አዛኝ መስሎ ለመቅረብ ይፈልጋል፡፡ የወገኖቻችንን ብልት በየወህኒ ቤቱ እንደማይጠብስ፤ በየመቱ በሺ የሚቆጠሩ ወገኖቻችንን ያለምንም ምክንያት፤ በአመለካከታቸው ስላልተስማሙት ብቻ እንደማያስር፤ አዲስ አመት ባበተ ቁጥር በሺዎች ከሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞቹ መሃል፣ ትኩረት ስበዋል ብሎ ከገመታቸው መሃል አንድ ሁለቱን ብቻ በመፍታት የመሃሪ ካባ ለመልበስ ይሞክራል፡፡ በዘንድሮው የአዲስ አመት በአል ከቤተሰባቸው ጋር ለመዋል ያልተፈቀደላቸው፣ በሺዎች የሚቆጠሩ የህሊና እስረኞች መኖራቸውን ሳናስብና፣ በዕንቁጣጣሽ ማዕዳችንም ፀሎት ወቅት ሳናስታውሳቸው ማለፍ አይቻለንም። በዝነኛው ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ መፈታት የተደሰትነውን ያህል ለ16 ወራት በግፍ መታሰሩ እያንገበገበን፣ ከአራት አመት ህፃን ልጇና ከምትጦራቸው እናቷ ተነጥላ በእስር ላይ የምትማቅቀውን የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር፣ ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳን ሳናስብ፤ ዘረኛነትን በመቃወማቸው በሚያንገፈግፍ ሰቆቃ ውስጥ እየተጠበሱ ያሉትን እነ ጀነራል ተፈራ ማሞን፤ ልጃችሁ ወይንም ወንድማችሁ ይቃወመናል ስለዚህም እነሱን ለመበቀል አጠገባችን ያላችሁትን እንቀጠቅጣለን በሚል የሚረገጡትን የ83 አመት አባት እነ አቶ ፅጌ ሀብተማርያምንና ሌሎቹንም የሕሊና እስረኞች ሳናስብ በአሉን ማክበር አይቻለንም።

የህሊና እስረኞቻችንንም በፀሎታችን ከማሰብ አልፈን ግን፣ ምን ብናደርግ ነው እንዲህ አይነቱን ተግባር ለአንዴና ለሁሌም ማስቆም የምንችለው? እነኝህን የሚሰቃዩ ወገኖቻችንንስ እንዴት ነው የምንታደገው? ብለን የምንወያይበት ጥሩ አጋጣሚ ነው እንላለን፣ ይህ የአዲስ አመት መባቻ ያቀረበልን እድል ።

*ውድ ወገኖቼ!*

*እነዚህ ሁሉ ከላይ የጠቀስናቸው የአዲስ አመት መባቻ ማሰላሰያዎች ግን፣ ከተራ ውይይት አልፈው የሃገራችንን የወደፊት ዕጣ በሚወስኑበት መንገድ ተግባር ላይ የሚውሉበት እድል ሊኖር ይገባል። ዘረኛውን ስርአት እንኳንስ በልመናና ልምምጥ፣ በ25 ሚሊዮን የህዝብ ድምፅም እንኳ ልንለውጠው እንደማይቻለን ግንቦት 97 አስተምሮናል። ምን ይሻላል? እንዴት ነው የህይወታችን ባለቤቶች ሆነን፣ ከዘረኛ መርዝ ምድራችንን የምናፀዳው?*

*አምባገነኖች ለፖለቲካ መፍትሄ ቁብም የላቸው ። ከስልጣን ጋር የተጎዳኘ ችግራቸውን ሁሉ በሙቶ ሺህዎች ባሰለፉትና ባስታጠቁት ጦራቸው የሚፈቱ ይመስላቸዋል ። ጦርነት ፖለቲካው የአመፅ ጎዳና ሲከተል የተወለደ መሆኑን ሊገነዘቡት ፈቃደኛ አይደሉም። ስለሆነም፣ በፖለቲካዊ እሰጥ አገባ መፍትሄ ሊያገኙላቸው ይችሉት የነበሩ ጉዳዮች ሁሉ አመፃዊ መፍትሄ እንዲወስዱ በማድረግ፣ ተቃዋሚዎቻቸውን ወደ ትጥቅ ትግል ይገፋሉ።*

***ይታያችሁ!** ድርጅታችን ግንቦት7ን ጨምሮ መላው የኢትዮጵያ ተቃዋሚም ሆነ አጠቃላይ ሕዝቡ እየጠየቀ ያለው እኮ በጣም ቀላልና መሰረታዊ የሆነ ነፃ ሰው የመሆን ጥያቄ ነው፡፡ እኛ አሁን እየጠየቅን ያለነው ሌሎች አገሮች ከሁለትና ሶስተ መቶ አመታት በፊት ያገኙዋቸውን መብቶች ነው፡፡ ከቅኝ ግዛት ከተላቀቁ ገና 40 አመት የሆናቸው እንደ ጋና ያሉ የአፍሪካ አገሮች ሕዝቦች ያገኙትን ነው እኮ እኛ በአያቶቻችን ደም በነጻነት ኖርን ለምንል ኩሩ ሕዝቦች የሚከለከለን፡፡ ጥያቄያችን ሰብአዊ መብታችን ይከበር ነው፡፡ ለቅሶአችን በመረጥነው መንግስት እንተዳደር ነው፡፡ ኤሎሄ የምንለው እንደ ዜጎች በእኩልነት እንታይ ነው! የለም እንደ ባርያ ረግጬ፤ ሱሪያችሁን አውልቄ በአርጩሜ እየገረፍኩ፤ እኔን ስታዩ በፍርሀት እየተርገፈገፋችሁ፤ እኔ ከናንተ ከተለየ ምርጥ ዘር የተፈጠርኩ መሆኔን ተቀብላችሁ ብቻ ነው በሰላም የምትኖሩት ነው እያለን ያለው! ወይ ሰላም በባርነት፤ አለበለዚያም አመፅ ለነፃነት ነው ምርጫችሁ እኮ ነው የሚለን!*

*በምርጫ 97 ማግስት፣ የተፈጠረውን ውጥረት ለማርገብ ብሎም ፖለቲካዊና ሰላማዊ መፍትሄ ለማግኘት በመለስ ቢሮ በተገኘንበት ወቅት፣ "ወይ አንገታችሁን ደፍታችሁ ፓርላማ ግቡ፣ ወይ ተሰደዱ፣ ወይ እንደ ወንዶቹ በረሃውን ሞክሩት" የሚለውን የመለስ እብሪተኛ "ግብዣ" ስሰማ የተሰማኝን ሃዘን በቃላት መግለፅ አይቻለኝም። በጠረጴዛ ውይይት ዙሪያ ለሃገሪቷ የፖለቲካ ችግሮች መፍትሄ ማግኘት ቢቻል እሰየው ነበር ። ሆኖም አልተቻለም።*

*ለመሆኑ ወያኔ በሕዝብ ፈቃድ ያላገኘውን ስልጣን እንዴት ለዘላለም ይገዌው እቆያለሁ ብሎ አሰበ? የዚህ ትእቢት ምንጮች ሁለት ይመስሉኛል፡፡ ሕዝቡን እርስ በእርሱ በዘር እንዲከፋፈልና ለአንድ አላማ እንዳይነሳ አባልቼዋለሁ የሚለው እምነቱና ባከማቸው የጦርና የስለላ ተቋዋማቱ በመመካት!*

*ለመሆኑ ወያኔ ችግሮቼን ሁሉ ሊፈታልኝ ይችላል ብሎ የሚመካበት የወያኔ ሰራዊት፣ እውን እንደሚነገረን መብረቃዊ ሃይል ነውን? ለምንድን ነው የወያኔ ዘረኝነት መንበርከኩ አይቀርም የምንለው? እንደሁሉም አምባገነኖች ወያኔም በአስገራሚ ሁኔታ ከትቢያ የመነሳቱን ያህል፣ በመጣበት አስገራሚ ሁኔታም መክሰሙ የማይቀር ነው ብሎ የግንቦት7 ንቅናቄ ያምናል ። ለምን?*

- *በመጀመሪያ አምባገነኖች ሁሉ አቅማቸው በጦር ሃይላቸው የመገንባቱን ያህል፣ ሕዝቡን ለማሳመን የሚችል የፕሮፓጋንዳ አቅማቸው ግን በጣም ደካማ ነው ። ምን ትኩረት ሰጥተው ብዙ ሚሊዮኖች ቢያፈሱበትም ይህን ሕዝብን ለማሳመን ያለመቻል ድክመታቸውን መወጣት አይቻላቸውም ። ምክንያቱም የፕሮፓጋንዳ ደካማነታቸው የሚመነጨው ከፀረ-ህዝብ ፖሊሲዎቻቸው ነው። የወያኔ የፕሮፓጋንዳ ክስረት እጅግ አስገራሚ ከመሆኑ የተነሳ፣ የተቃዋሚ ሃይሎችን ድምፅ ማዳመጥ በሽብርተኝነት ያስከስሳል ብሎ እስከማወጅ አድርሶታል ። በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር በሚቆጣጠረው ሚዲያ የሚያስተላልፈውን አይን ያወጣ ውሸት የሚሰማው ቢያጣ፤ ሌላ ምንም ነገር መስማት አትችሉም ይላችሁዋል፡፡ ይህ እንግዲህ፣ የደርጉ ወታደራዊ አምባገነንነት በመጨረሻ ቀናቱ እንኳ ሊያውጅ ያልደፈረው መሆኑን ስናይ የስርአቱን መናጋት ጥልቀት ያበስርልናል ።*

- ሁለተኛ የደርጉ ሰራዊት አንዱ ድክመት፣ ሹመት በችሎታና እውቀት፣ በጦር ሜዳ ጀግንነት የሚገኝ ብቻ ሳይሆን፣ በታማኝነትና አድርባይነትም የሚታፈስ ስለነበር፣ ለሰራዊቱ የሞራል መላሸቅ ብሎም ሽንፈት ታላቅ አስተዋፅኦ አድርጎ ነበር ። ከምርጫ 97 ሽንፈት ወዲህ ወደዘረኛ አደረጃጀት ፊቱን የመለሰው ወያኔ፣ የጦር ሰራዊቱን ሹመት እንደ ደርጉ ዘመን በታማኝነት እንኳ የሚገኝ ሳይሆን፣ ከዚያም በባሰ ኢሞራላዊና ዘረኛ በሆነ መንገድ፣ ለትግራይ መኮንኖች ብቻ የሚታደል ማድረጉ፣ ይህን እምቢ ብሎ በሚነሳ የነፃነት ጥማተኛ ፊት እንደ ጉም ሊበን የሚችል ሰራዊት ያለው ለመሆኑ ከቶ አጠራጣሪ አይደለም ። በሶማልያ የታየው ሽንፈቱ የጠቆመን ነገር ቢኖርም ይህን ውስጣዊ ድክመቱን ነው ።

- ሶስተኛ ከደርግ ሠራዊት ድክመቶች አንዱ ከፍተኛ መኮንኖቹ በቅንጦት ህይወት የታጠሩና፣ ይህንንም የኑሮ ዘይቤአቸውን ለመደጎም፣ ከመከላከያ በጀቱ የሚያሸሹበት ቀዳዳዎች ብዛት የትዬለሌ መሆኑ ነበር።  ይህም በሃገራዊ ብሄርተኝነት ተቃጥለው ለኢትዮጵያ አንድነት ለመሰየፍ በየጦርሜዳው ተሰልፈው የነበሩት ወታደሮችና የመስመር መኮንኖች ላይ የነበረው የሞራል ጫና ከፍተኛ ነበር ። ሆኖም ይህ የደርጉ የበላይ መኮንኖች "የቅንጦት ህይወት" ከዛሬው የወያኔ ኮሎኔሎችና ጄኔራሎች ቅብጠት ጋር ሲወዳደር፣ ለካ የደርጉ መኮንኖች ባህታውያን ነበሩ የሚያሰኘን ሆኖ አግኝተነዋል። በእንዲህ አይነት ቅንጦት ውስጥ የሚኖሩ የበላይ መኮንኖች ለመስዋዕትነት ተግተው፣ ሰራዊቱንም ለድል ያበቃሉ ብሎ ማሰብ፣ ከአምባገነኖች አዕምሮ ብቻ ሊፈልቅ የሚችል ተራ ድንፋታ ነው ።

- አራተኛ የግንቦት 83 የወያኔ ድል በውስጣዊ አደረጃጀት ብቃቱ፤ በታጋዮቹ የአላማ ፅናት፣ በመሪዎቹ የስትራተጂ አሳቢነት የተገኘ ድል አልነበረም። ትግሉ በትግራይ ክልል ውስጥ በነበረበት ወቅት "ትግራይን ከብሄራዊ ጭቆና ነፃ አደርጋለሁ" በሚለው አላማው በሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶችን ማሰለፍ ችሎ ነበር። ይህ ለጠባብ ብሄርተኛ አላማ የተመለመለ ወጣት ግን የጉናን የደብረታቦርን ወዘተ ጦርነቶች መቋቋም ባለመቻሉ፣ 25 ሺህ ጦር ወደትግራይ መልሱኝ ብሎ ሸሽቷል ። በጊዜው የሶቭየት ሕብረት መሪ የነበረው የጎርባቾቭ ግላሸኖስት ብሎ የጀመረው የለውጥ ፖሊሲ በደርጉ ላይ ያሳደረው መነጠል፣ የሻዕቢያ ስትራተጂክ መልሶ ማጥቃትና ድል በፈጠረው ምቹ ሁኔታ ተጠቅሞ ከመዲናው የዘለቀ ጦር ነው። ወያኔዎች እንደሚያወሩት እንደ ትግራይ አማራውን ኦሮሞውን ደቡቡን አደራጅቶና የህዝብ ድጋፍ አግኝቶ ያሸነፈ ጦር አይደለም። አሁን ያለውማ ጦር በዘር ተከታትፎ ለማን እንደሚሞትም የሚያውቅ አይደለም፡፡ ይህ አሁን ያለው ጦር ከኢትዮጵያ የነፃነት አርበኞች ጋር ለመዋጋት የሚያስችለው አላማ የለውም ። "ፀረ-ትግሬ ኢንተር ሃምዌዮች መጡብህ" እየተባለ በቀላሉ የሚደለል ጦር አይደለም፡፡ የመሪዎቹን ውሸት በሚገባ አውቆታል፤ በሶማሌም አይቶታል፡፡ ነገ የኢትዮጵያ የነፃነት ሃይሎች ፀረ-ትግራይ አለመሆናቸውን ብቻ ሳይሆን፣ በብሄረሰቦች እኩልነት የሚያምኑ፣ የየትኛውም ብሄር ልሂቅ የበላይነት የማይኖርበት ስርአት ለመገንባት የሚታገሉ መሆናቸውን ሲያውቅና እርሱም ለህገ መንግስቱ ብቻ ለሚገዛ ሃገራዊ የመከላከያ ሃይል ተጨማሪ ክንድ ለመሆን እንደሚችል ሲረዳ፣ ዘረኛው ስርአት ላይ አፈሙዙን እንደሚያዞር ቅንጣት ጥርጥር ሊኖረን አይገባም ።

- አምስተኛ ወያኔን የመሰረቱ፣ በኮማንደርነት ያገለገሉ፣ የጦር እቅድ የነደፉ፤ ቢያንስ የሚታገሉበትን መርህ የሚያውቁና የሚያምኑ ከፍተኛ መሪዎቹ በውስጡ በደረሰው መከፋፈልና በሞት የተነሳ ትተውት ሄደዋል። ስልጣን ከያዘ ወዲህም ያካበተው ልዩ የወታደራዊ አመራር ብቃት የለውም። ለደርግ ውድቀት ትልቁን አስተዋፅኦ ካደረጉት ነገሮች አንዱ፣ በውጊያ የተፈተኑ የመስመር መኮንኖች እጥረት ነበር። በሶማልያ የታየውም የወያኔ ዝርክርክነትና ሽንፈት፣ በአንድ ጎኑ በጎጠኛ ወንድማማችነት የተሾሙ፣ ግን ለቦታው የማይመጥኑ መኮንኖች የነበሩት መሆኑ ነበር ።

የወያኔ ዘረኛ ስርአት በውስጡ የተወሳሰቡ ችግሮች ያሉት ሃይል መሆን ብቻውን ግን ለአስተማማኝ ድል ያበቃናል ማለት አይደለም። የወያኔ ድክመትና ውስጣዊ ድቀት፣ በኢትዮጵያ ነፃነት ሃይሎች ጥንካሬ መታጀብ አለባቸው ። የታጋዩ ሃይል አስተማማኝ ጥንካሬዎችስ ምንድን ናቸው?

- ከሁሉም ነገር በላይ እፁብ የሆነ በሃገራዊ አንድነት፣ የብሄረሰቦች እኩልነትና፣ የዴሞክራሲያዊ መንግስት ምስረታ አላማ አለው። ዘረኛ አምባገነንነትን አምበርክኮ፣ ከህዝብ ልብ የተቀዳ ብሄራዊ መንግስት ለማቆም የቆረጠ ህዝባዊ አላማ አለው። ይህም አላማ፣ ከእያንዳንዱ ዜጋ ህልምና ምኞት ጋር በብዙ ሸህ ጅማቶች የተሳሰረ ነው። በምርጫ 97 አፈና ድምፁን የተቀማው ህዝብ ሁሉ፣ ዘላቂ ሰላምና ልማት፣ በፈቃዱ ከመሰረተው ህዝባዊ መንግስት ውጪ ሊገኝ እንደማይችል ተምሯል ።

- የኢትዮጵያ የነፃነት ሃይሎች "ስልጣን ከጠብመንጃ አፈሙዝ ይፈልቃል" በሚል ርዕዮተአለማዊ እምነት አመፅን የመረጡ ሳይሆኑ፣ ለ18 አመታት ወያኔ ለህዝብ ፍላጎት ራሱን ተገዥ እንዲያደርግ ሲማጠኑ፣ ሲለምኑ፣ በአለም መንግስታት ሸንጎዎች ጭምር ሲያነቡ ከርመው፣ አማራጭ በማጣትና በመገፋት የመረጡት የራስን መከላከል እርምጃ ስለሆነ፣ ጥልቅ በሆነ ዕምነትና፣ እንደ ብረት በጠነከረ መሰረት ላይ የገቡበት የትግል ስልት በመሆኑ፣ አርበኝነቱ ወደር የማይገኝለት እንደሚሆን አልጠራጠርም፡፡ በዚህ ኢትዮጵያዊ ወኔ ፊት የሚቆም የዘረኛ ጦር ሊሰነብት ከቶ አይቻለውም ።

- ባለፉት 35 አመታት መጠነ ሰፊ የሆኑ ወታደራዊ ግብግቦች በሃገራችን ተካሂደዋል። በሚሊሺያነት፣ በወታደርነት ከዚያም አልፎ በመኮንንነት...ወዘተ ተሰልፎ ወታደራዊ ልምድ ያካበተው ኢትዮጵያዊ የትየለሌ ነው። ወያኔ አዲስ አበባ ከገባ በኋላ ብቻ እንኳን ከወታደርነት የተገለለውና፣ በውርደት የተባረረው የመደበኛ ጦር አባል ከ325 ሺህ በላይ ነበር። በኤርትራ ጦርነት ጊዜ አገራቸውን ያገለገሉ ብዙ ኢትዮጵያውያን ተባራሪ ወታደሮች ሞልተዋል፡፡ ኢትዮጵያ የመሳሪያ፣ የዕውቀት፣ የአሰልጣኝ፣ የጦር መኮንኖች ችግር የለባትም። "ና ለሃገርህ አንድነትና ከወገኖችህ ልቦና ለሚፈልቅ መንግስት ምስረታ ተዋደቅ!" ብሎ ጥሪ የሚያደርግለት አመራር እስካለ ድረስ፣ በአዎንታ የሚመልሱ የሰለጠኑ ኢትዮጵያውያን ብዛት ባህር ነው ።

- በኢትዮጵያ ለውጥ ለተጠሙ ሃይሎች ጥሪ የጎረቤት ሃገሮች ምላሽ የሚያበረታታ ነው ። የሱዳን፣ ኤርትራ፣ ሱማሌ ድንበሮች ለታጋዮች ክፍት ናቸው ። በሰሜን ሱዳን በኩል የኢትዮጵያን መሬት በመቁረስ፣ የጄኔራል በሽርን መንግስት ወዳጅነት ሊያማልል የሞከረው ወያኔ፣ ደቡብ ሱዳንን ለማስገንጠል ከባእድ ሃይሎች ጋር እጅና ጓንት ሆኖ እየሰራ መሆኑን የሱዳን መንግስት ከተረዳ ውሎ አድሯል ። ወያኔ ከጠባብ ጎሰኝነቱና አድርባይነቱ ውጪ የሚሰየፍለት መትከል የሌለው መሆኑን ጎረቤቶቹ ሁሉ ተረድተው፣ ለማይቀረው ስንብቱ ድጋፋቸውን ለመስጠት ዝግጁ ናቸው ።

- በአሜሪካ የባራክ ኦባማ መመረጥ የፈጠረው ተጨማሪ ዕድልም አለ ። አምባገነኖች ቡጢያቸውን እንዲያላሉ ፕሬዚዳንቱ ቃለ-መሃላ በፈፀሙበት ዕለት ያሰሙት ተማፅኖ፣ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲውን የመቅረፅ አቅም እንዳለው እየታየ ነው ። ከምርጫ 97 በሁዋላ ደግሞ ብካይና አፈናን በማበራከት መግዛት እችላለሁ ብሎ የቆረጠው ወያኔ፣ ጡንቻውን እንዲያላላ እየተጠየቀ ነው ። የወያኔ ዘረኛ ስርአት የዋሽንግተን ጠበቃና እንደራሴ የሆነው ዲክ አርሚ ፕሬዚደንት ኦባማ የሚደግፉትን ለድሀው የጤና ዋስትና የሚሰጠውን የጤንነት ማሻሻያ ፕላን "ነብሰ ገዳይ ፕላን ነው" እያለ በፀረ-ህዝብነት የተሰለፈበት ወቅትም ስለሆነ፣ የወያኔ ሰልፍ ከነማ ጋር እንደሆነ ግልፅ ሆኗል። የምርጫ 97 የህዝብ ድምፅ መሰረቅ ከአፅናፍ አፅናፍ ያንቀሳቀሰው በውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ፣ በተቃዋሚ ድርጅቶች አመራሮች ውስጥ በተፈጠረው አለመግባባት አዝኖ የነበረ ቢሆንም፣ ለጊዜያዊ እክሎች ዘላቂ ሃገራዊ ጥቅሙን አሳልፎ መስጠት እንደሌለበት ተረድቶ፣ የምእራባውያንን የስልጣን ደጃፎች እንደገና ማንኳኳት ጀምሯል። አዲስ የዲፕሎማቲክ ጥቃት ለመጀመር፣ ዝግጅቱ በመጠናቀቅ ላይ ነው ።

በሌላ በኩል የወያኔ በስልጣን የመቆያ አንድ መሳሪያ ሆኖ ሲያገለግለው የቆየውና የሚመካበት ሕዝቡን በጎጥ ከፋፍየዋለሁ፤ አብሮ አይነሳብኝም፤ የሚለው ቁማሩም፤ በውሸት ብዛት እየተነነበት ነው፡፡ ወያኔ ያልነከሰው የዘውጌ ማህበረሰብ የለም፡፡ ስለብሄረሰብ እኩልነት ማውራትና የሰዎችን እኩልነት በተግባር መቀበል ለየቅል መሆናቸውን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ያወቀበት ደረጃ ላይ ደርሶአል ማለት ይቻላል፡፡ በዘርና በቋዋንቋዋ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ ብዙ ሳይቆይ የጎጥና የመንደር ፖለቲካ እንደሚሆንና እርስ በእርስ እንደሚያባላ እርስ በእርስ በምትተራመሰው ሶማልያ ብቻ ሳይሆን እዚሁ እኛ አገር በወያኔ በራሱ ውስጥ የሚካሄደውን መንደርተኛነት የሚመለከት ሁሉ ያውቀዋል፡፡ የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ክርፋት፤ በዘር ላይ የተመሰረተ ፖለቲካን ሁዋላ ቀርነት ብቻ ሳይሆን ፍፁም የሕብረተሰብን ችግር በእኩልነት መፍታት የማይችል፤ ግፋ ቢል የአገሪቱን ሀብት ለመዝረፍ ማነው ተረኛው ዘውግ ወደሚል ማለቂያ የሌለው ገደል የሚከት አደገኛ አካሄድ መሆኑን ሁሉም የአገሪቱ ዘውጌ ማህበረሰባት ከዚሁ ከወያኔ የ18 አመታት አገዛዝ ያወቁበት ጊዜ ነው፡፡ ለዚህ ነው የተለያዩ ዘውጌ ማህበረሰባትን ወክለው ወያኔን እየተዋጉ ያሉ ሀይሎች (የትግራይ የእኩልነት ታጋዮችን ጨምሮ) በጋራ ሆነው ለሁሉም እኩል የሆነች ኢትዮጵያን በጋራ መገንባት ብቸኛው መፍትሄ መሆኑን እየተቀበሉ የመጡት! ከዚህ በፊት አይንህን ላፈር ሲባባሉ የቆዩ፤ በምንም አይነት አብረን በአንድ አገር መኖር አንችልም ሲሉ የነበሩ ሀይሎች፤ የሙብቶችን ሙሉእነት ተገንዝበው፡ በጊዜያዊነት ወያኔን ለማስወገድ ብቻ ሳይሆን የጋራ ራዕይ ሰንቀው፤ ለጋራ ትግል አብረው እየመከሩ ያለበት ጊዜ መሆኑን ስለምናውቅ ነው የወያኔ እድሜ እጅግ እያጠረ መሆኑን በልበሙሉነት የምንናገረው፡፡

እነዚህ ሁሉ ከላይ የጠቀስኳቸው ሁኔታዎች የዘረኛውን ወያኔ ክስመት የህዝባዊ ሃይሎችንም አይቀሬ ድል የሚያበስሩ ናቸው ። ለውጡ ዕውን እንዲሆን ግን፣ ትንተናው በተግባር መፈተሽ አለበት። የግንቦት7 ንቅናቄ ደጋግሞ ለማስጨበጥ እንደሞከረው፣ የአሁኑ ትግል እንደ ጥንቱ ከአንድ ማዕከልና፣ በአንድ ማዕከላዊ አመራር የሚካሄድ አይሆንም። በዜጎች ነፃነት ላይ ተመስርቶ፣ እያንዳንዱ ዜጋ በግልና በሚተማመንበት ስብስብ፣ "ምን ባደርግ ነው የዚህን ስርአት ህልፈት ማቃረብ የምችለው" ብሎ ሊያስጠነቅር በቻለው አቅምና ጥልቀት የሚወሰን ነው። ከአንድ ግንባር የሚገፋ ሳይሆን፣ በብዙ ሺህ ግንባሮች በተናጠልና በቅንጅት የሚካሄድ ህዝባዊ አመፅ ነው። ወያኔ ጆሮው ሲቆም የሚተኛ፣ ተደላደልኩ ብሎ ሲያርፍ የሚቆነጥጥ፣ የግብረ ጉንዳን ገድል ነው የሚሆነው ። ከተማና ገጠርን አይለይም፣ ወንድና ሴት አያማርጥም፣ ሃገርቤት ያለና በውጭ የሚኖር ብሎ አይከፋፍልም፣ በአንድ ወቅት ሁሉምጋ ና የትም የሚገኝ ነው ። ድንበር ዘለልም ነው የሚሆነው።

***ውድ ወገኖቼ፡***

በቅርብ ጊዜ ከአገር ቤት ለእረፍት የወጣ አንድ ባለፀጋ ወዳጄ ካለሁበት ቦታ ፈልጎ በስልክ አግኝቶኝ አገሪቱ ያለችበትን በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ፤ የወያኔ ዘረኛነት የደረሰበትን አይን አውጣነት፤ በነጋዴው ላይ የሚደረገውን አይን ያወጣ ዘረፋ፤ የኑሮ ውድነት የፈጠረውን ዘግናኝ ሁኔታ፤ በፍፁም መኖር የማይቻልበት ሁኔታ ላይ እንደተደረሰ በምሬት ሲነግረኝ ቆይቶ፤ አሁን ተስፋችን ያለው እናንተ ጋር ነው፡፡ አድኑን! ድረሱልን! እያለ በተማፅኖ ይነግረኛል፡፡ በጥሞና ከሰማሁት በሁዋላ፤ እሺ እኛስ የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ቃል እንገባለን፡፡ ለመሆኑ አንተስ ይህን ያንገሸገሸህን አገዛዝ ለመጣል በሚደረግ ትግል ምን አስተዋፅኦ ታደርጋለህ? ብዬ ስጠይቀው ለአንድ ሰኮንድ እንኳዋን ሳያስብ፤ እንዴ እኛማ ምን እናደርጋለን! ጥዋት ማታ በፀሎት አብረናችሁ ነን! ያለን አቅም ፀሎት ብቻ ነው! ይለኛል፡፡

ሁለት ነገር ነው ወዲያውኑ በአዕምሮዬ ውስጥ የመጣው፡፡ የመጀመሪያው ይህን ወዳጄን በደንብ አውቀዋለሁ፡፡ በጣም ታታሪ ሰራተኛ ነው፡፡ ንብረት ለማፍራት፤ ልጆቹን በጥሩ ሁኔታ ለማስተማርና ለማሳደግ ሲማስን ነው የሚውለው፡፡ ፀሎት የሚያደርገውም ሰርቼ፤ ደክሜ፤ ያፈራሁትን ንብረት ባርክልኝ፤ ጠብቅልኝ ብሎ እንጂ ፈጣሪውን እኔ ቁጭ ብዬ ስፀልይና የአንተን ስም ሳሞግስ እውላለሁ፤ አንተ ንብረት ስጠኝ ብሎ አይደለም፡፡ ንብረቱማ በስራ እንደሚገኝ አውቆ ነው ሲባዝን የሚውል፡፡ ታዲያ የነፃነት ጉዳይ ሲሆን፤ የመብት ጉዳይ ሲሆን፤ የክብር ጉዳይ ሲሆን፤ የአገር ጉዳይ ሲሆን፤ እንዲያው ዝም ብዬ ስለፀለይኩ ይገኛል ብሎ እንዴት አሰበ? ፀሎት ጥሩ ነገር ነው፡፡ ግን ፈጣሪም እኮ እየሰራችሁ ለምኑኝ ነው ያለው፡፡ የሱ አባቶች በአንድ እጃቸው የሀይማኖት መፅሀፋቸውን፤ በሌላ እጃቸው ጦራቸውን ይዘው እንደሆነ ጣልያንን ያሸነፉት ያውቃል፡፡ ወይንስ የገንዘብ ማካበቱንና ጥሩ ኑሮ የመኖሩን ስራ ለራሱ፤

ለሱ ነፃነት የሚደረገውን ትግል ግን ሌላ ሰው እንዲያደርግለት ነው የሚፈልገው? ፈጣሪውስ በርግጥ በዚህ አካሄድ አያዝንበትም? የሚለውን ነበር የማስበው፡፡ በሌላ በኩል ግን ለምንድን ነው እያንዳንዱ ሰው ምንም አቅም የለኝም፤ ለለውጡ ምንም የማግዘው ነገር የለም፤ ምንም ችሎታ የሌለኝ ከንቱ ነኝ ብሎ እንዲያስብ የሆነው የሚለውን ነበር የማሰላስለው፡፡

በርግጥ ለብቻ ከመታገል በጋራ መታገል፤ በግለሰብ ከሚደረግ እንቅስቃሴ የተደራጀ እንቅስቃሴ የላቀ ውጤት ያመጣል፡፡ ድርጅት ሀይል ነው የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ማለት ግለሰቡ ምንም ለማድረግ አይችልም፤ ምንም አስተዋፅኦ ማድረግ አይችልም ማለት አይደለም፡፡ አንድ ሰው ከቆረጠ፤ ካመነበት፤ ነፃነት ማጣቱ ካንገበገበው፤ ውርደቱ ከሚሸከመው በላይ ከሆነበትና፤ በጀብደኝነት ሳይሆን በብልሃት ከተንቀሳቀሰ፤ ተደራጅቶ መታገል እንኳዋን ባይችል በግሉ ከራሱ ጋር ተማክሮ የሚወስዳቸው እርምጃዎች ይህንን ዘረኛ ስርአት ለማንበርከክ በሚደረገው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ የራሱን አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል፡፡ እነኝህ በግለሰብ ደረጃ የሚደረጉ አስተዋፅኦዎች፤ ከተደራጀ ሕዝባዊ አመፅ ጋር ተደማምረው ነው ይህን ዘረኛ አገዛዝ የሚያሽመደምዱት፡፡

**ውድ ኢትዮጵያውያን!**

የግንቦት7 ንቅናቄ ሁለገብ የሆነ የትግል ስልት ተመራጭ መንገድ ነው ብሎ ተቀብሏል። ሁለገብ ሲልም ከግለሰብ ውስጥ ከሚፈልቅ የእምቢተኛነት እርምጃ ጀምሮ ሌሎች የተቀናበረ የሰላማዊ ትግል ስልትንም ያካትታል ። ወያኔ አምባገነንም እንኳ ሆኖ፣ ሃገራዊ ብሄራዊ ጥቅምን የተረዳና፣ መሻገር የማይገባቸውም የዜጎች መብቶችና ክብሮች መኖራቸውን የተረዳ መንግስት ቢሆን ኖር፣ ሰላማዊ ህዝባዊ ትግልን ቀዳሚና ዋነኛው አድርገን በወሰድን ነበር ። ሆኖም ወያኔ ከኖረበት ጠባብ ብሄርተኝነቱና ፀረ-ኢትዮጵያ እምነቱ በመነጨ፣ ስልጣንን በአናሳ አገዛዙ እጅ ለማቆየት፣ የማይፈነቅለው ድንጋይ የማይበጥሰው ቅጠል እንደሌለ፣ በእስራታችን በክብራችን መዋረድና እንግልታችን ወቅት፣ የስለላ አባሎቻቸውን አክታ ከፊታችን እያበሰን ሞክረነዋል። ወያኔና ጀሌዎቹ ለማንም ምንም ክብር የሌላቸው ውርጋጦች ስብስብ መሆኑን ሰሞኑን የቀድሞውን ፕሬዜዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን ለውይይት በተጠራ ሕዝባዊ ስብሰባ በጠራራ ፀሀይ በአዳማ ከተማ ላይ ያደረጉትን ያየ ሊጠራጠር አይችልም፡፡ አሁን ስለ ሰላማዊ ህዝባዊ ትግል ስንናገር፣ ሌላው የነፃነት ታጋይ በዱር በገደሉ ሲዋደቅ፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ኑሮውን እየኖረ ልጆቹን እያሳደገም፣ እንዴት የዘረኛ አገዛዙን ዕድሜ ማሳጠር እንደሚቻለው ለማመላከት ነው ።

አምባገነኖችን በስልጣን እንዲቆዩ የሚረዳቸው፣ የህዝቡ ሰላማዊ እምቢተኛነት ደካማ መሆን ነው። አምባገነኖች ሁሉንም ሰው ልክ እንደነሱ ለሆዱ የሚገዛ አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ ስለዚህም ወይ በእንጀራው እንመጣበታለን፤ ወይ እናስፈራራዋለን፤ ወይም ቅስሙን ሰብረን እንገዛዋለን ብለው በትንሽ ጭንቅላታቸው ያስባሉ፡፡ ይህን ትግል ከዳር ለማድረስ ከሚያስፈልገው ጉዳይ አንዱ ይህ የአምባገነኖች ስሌት ስህተት መሆኑን እራሳችንን ላላስፈላጊ አደጋ ሳናጋልጥ፤ በውስጥ አንጀታችን ከተቋዋጠረ የነፃነት እልህ ጋር በምንም አይነት እኛንው ረግጦ ለመግዛት አንተባበረውም ብሎ ወስኖ በግል ለዚህ ዘረኛ መንግስት ትብብር መንፈግ ነው፡፡

**ውድ ወገኞቼ!**

ይህ የዛሬው የአዲስ አመት መልእክት የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የመጨረሻው መጀመሪያ እምቢልታ የተነፋበት ነው፡፡ ባጠቃላይ ከሀዘንና ከንፈር ከመምጠጥ ወጥተን እያንዳንዳችን በተግባር ትንሽም ብትሆን ጠጠር የምንወረውርበት ጊዜ መጀመሪያ ነው፡፡ በያካባቢው የሚገኙ የነፃነት ታጋዮች የሚያደርጉትን በእንቅስቃሴያቸው ታያለህ፡፡ የምትችል ሁኔታህን ካመቻቸህ በሁዋላ ተቀላቀላቸው፡፡ የማትችል መረጃ በማቀበል፤ ቢጠማቸው ውሀ በማጠጣት፤ ቢርባቸው በማብላት መደበቅ የሚፈልጉትን በመደበቅ ተባበራቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግን በራስህ ከዚህ የሚከተሉትን እርምጃዎች በግልፅ ሳታወጣ/ሳታወጪ በውስጥህ/በውስጥሽ ወስነህ/ወስነሽ በግልህ ውሰድ/ውሰጂ፡

1. ከማናቸውም የወያኔና የተለጣፊዎች የፓርቲ የንግድ የዝርፊያ ድርጅቶች፤ ወይንም በግለሰብ ስም እያደርጉ ከሚዘርፉት ድርጅቶቻቸው፤ ወይንም ከታወቁት ከነሱ አጋር ነጋዴዎች ጋር ምንም አይነት

የንግድ ውልም ሆነ የምርት መጠቀም አታድርግ፡፡ የነሱን ቢራና ለስላሳ ከምትጠጣ፤ ለነፃነትህ ውሀ ጠጣ፡ እነሱ ያመረቱትን ከምትለብስ የተቀደደ ልብስ ልበስ፤ በነሱ ሲሚንቶ ከምትገነባ ሆን ብለህ ሌላ መንገድ ፈልግ ወይንም ግንባታውን ለጊዜው ተወው፡፡ ይህንን ለራስህ ከውስጥህ ቁረጥ፡፡ ሌላው እስኪያደርገው አትጠብቅ፡፡

2. የመንግስት ሰራተኛ የሆንሽው በስራሽ ላይ ለግሚ፤ በቀን ሰርተሽ የምትጨርሺውን ስራ ሳምንት አቆይው፡፡ በመስሪያ ቤትሽ የሚደረገውን ዘረፋ፤ ሚስጥር ወይንም ማናቸውም ይጠቅማል ብለሽ የምታስቢውን መረጃ አንቺን በማያጋልጥ መልኩ ለነፃነት ታጋዮች አሳልፊ፡፡

3. እያንዳንዱ ነፃነቱን የሚናፍቅ፤ ዘረኝነት ያንገሸገሸው ኢትዮጵያዊ በከተማም ሆነ በገጠር በቅርብ ከሚያውቃቸውና ከሚያምናቸው ጉዋደኞቹ ወይንም ዘምዶቹ ጋር ብቻ በመሆን ከሶስት እስከ አምስት እራሱን ሆኖ ህዋስ ይፍጠር፡፡ ይህ ህዋስ ዝም ብሎ ስለአገሩ ጉዳይ ምን ማድረግ እንችላለን ብሎ የልቡን የሚወያይበት፤ በነፃነት ታጋዮች መገናኛ ብዙሀን የሚሰማውን ዜና የሚወያይበት፤ የሚቀርቡ ተግባራዊ ጥሪዎችን ተከታትሎ ምንም ሳይናገር ባካባቢው ተግባራዊ መሆናቸውን የሚከታተልበት፤ የአካባቢውን መረጃ ለነፃነት ሀይሎች የሚያቀብልበት በማህበራዊ ኑሮው የዘረኝነትን ሰንኮፍ የሚነቅልበት ህዋስ ነው፡፡ ግለሰቡ ብቻውን አለመሆኑን የሚያውቅበት፤ በዚህም ልበ ሙሉነት የሚያዳብርበት ነው፡፡ በእነኝህ ህዋሶች ውስጥ ያሉ ሰዎች ለምሳሌ በየሳምንቱ ትንሽ ሳንቲም እያዋጡ አንድ ቦታ ማስቀመጥ ይችላሉ፡፡ ይህን ሳንቲም በየጊዜው እንደሚፈጠረው ባካባቢያቸው በግፍ ሰው ሲታሰር፤ ወይንም በደል ሲደርስበት ከዚህ ከሰበሰቡት ገንዘብ የተበዳዩን ቤተሰቦች የሚረዱበት፤ ለነፃነቱ ሲታገል ቤተሰቡ እንዳይጎዳ ድምፃቸውን አጥፍተው አለንልህ የሚሉበት ወይንም ሌላ ለወደፊቱም ቢሆን ማህበራዊ እሴቶቻችንን የምናዳብርበት ይሆናል፡፡

4. አምነህበት ሳይሆን ለኑሮ ብለህ ወያኔ/ኢሕአዴግን የተቀላቀልክ፤ በተለይ አባል ካልሆንክ ስራ አትሰራም ተብለህ በውዴታ ግዴታ የገባህ፤ በግልህ ልብህ የሚፈልገውን በነፃነት የመኖር ጥም ለማርካት ከነፃነት ሀይሎች ጋር ብዙ ልትተባበር ትችላለህ፡፡ ከሌላውም የበለጠ የማታምንበት ድርጅት ውስጥ በማስገባት ያዋረዱት አንተን ነውና ውርደትህን በሆድህ ይዘህ፤ እልህህን እነሱን ለመገዝገዝ ተጠቀምበት፡፡ በመጀመሪያ ባካባቢህ የሚገኙ ዜጎችን አትበድል፡፡ አባል በመሆንህ የምታገኛቸውን ሚስጥሮች አሳልፍ፤ የነፃነት ሀይሎች አደጋ ላይ የወደቁ ሲመስልህ አስታውቃቸው፡ በአካባቢህ ከሚኖሩ ዜጎች ጋር የሰላምና የመተሳሰብ ኑሮ ኑር፡፡

5. የኢትዮጵያ ወታደሮች፤ ፖሊሶች፤ ደህንነቶች ወይንም ማናቸውም ይህን ዘረኛ መንግስት መስሎአችሁም ሆነ ተገዳችሁ የምታገለግሉ ኢትዮጵያውያን፡፡ ዘረኛነት በቃን በሉ፡፡ ለነፃነት፤ ለእኩልነት፤ ለአገር ክብር በሚታገሉ ወገኖቻችሁ ላይ በትር አታንሱ፡፡ በኢትዮጵያ ድሀ ህዝብ ታክስ እየተከፈለህ ጥቂት ዘረኞችን በስልጣን ለማቆየት ብለህ ከወገንህ ጋር ዘላቂ ቂም ውስጥ አትግባ፡፡ ለፖለቲካ ችግሮቻችን ፖለቲካዊ መፍትሄ እንዳንፈልግ በትእቢት ሁሉንም ረግጠን እንገዛለን ብለው የሚመኩት አንተን ከወገንህ ጋር ደም በማቃባት ነው፡፡ ነገ ዕጣህ እንደ ቀድሞዎቹ “የደርግ ወታደሮች” ሜዳሊያህን በየቤተ-ዕምነቱ ደጃፍ አንጥፈህ መለመን እንዳይሆን፣ “እኔ የህገመንግስቱ ዘብ እንጂ የወያኔ አሽከር አይደለሁም” ብለህ እምቢ በላቸው፡፡ የነፃነት ሀይሎችን፤ የእኩልነት ሀይሎችን እርዳ፤ ተቀላቀል! ለዘረኞች ስልጣን ብለህ አትሙት!

6. ለዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ መወለድ ጉልህ ሚና ከሚጫወቱት መሃል፣ የሙያ ማህበራት፣ የዖታ ድርጅቶች፣ የመፅሃፍት ክበባት፣ የወጣትና የተማሪዎች ማህበራት፣ የሰራተኞች ማህበራት ወዘተ ናቸው ። እነዚህ ስብስቦች ደግሞ የታለመላቸውን የዜጎች ነፃነት ግብ እንዲመቱ፣ ከአምባገነኖቹ ቁጥጥር ነፃ መሆን ይኖርባቸዋል ። በነፃነት የሚንቀሳቀሱ ማህበራት ምን ተአምር ሊፈጠሩ

እንደሚችሉ ለማወቅ፣ እግራችን እስኪነቃ መሰደድ አይኖርብንም ። በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ የተማሪው ንቅናቄ የፈፀመውንና፣ በምርጫ 97 ወጣቶች በነፃነት ሲያስቡ ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ አሳይተዋል፡፡ እነዚህ ተምሳሌቶችም፣ አሁንም ልንደግማቸው እንደምንችል ያበረታቱናል። ለነፃ ማህበራት ውሱን ግቦች የምናደርጋቸው ትግሎች፣ የዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ መፀነስና ብሎም ነብስ መዝራት ላይ ታላቅ አጋዥ ሃይሎች ናቸው ። ስለሆነም ትኩረት ሰጥተን ልናበረታታቸው ይገባል ። ሰላማዊ የትግል መንገዶች ስለሆኑ ከዜግነት መብት የሚመነጩ ናቸው ። ሆኖም ዘረኛው አገዛዝ ዝም ብሎ ያያቸዋል ማለት አይደለም ። ሊቆጣጠራቸው አለመቻሉን ሲያውቅ፣ ወደ አመፅ መሸጋገሩ አይቀሬ ነው ። ሰላማዊ የህዝብ ትግልን በአመፅ በመተረ ቁጥር ግን፣ በራሱ አባላትና በደህንነትና የጦር ሃይሉ ውስጥ ጥያቄና ተቃውሞ ሳይቀሰቅስበት ሊያደርገው አይቻለውም ። በመሆኑም፣ ጠላትን መከፋፈልና ማዳከም ላይ ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ። በዚህ የአዲስ አመት በአል ጅማሮ ላይ፣ ኢትዮጵያውያን፣ በመስሏቸው የሙያና በፍላጎቶች ዙሪያ በተሰባሰቡ ድርጅቶች ዙሪያ ዜጋዊ ነፃነታቸውን አስከብረው፣ በሃገራዊ ጉዳዮችም ሆነ፣ በተናጠል ነገሮች የመምከርና ድርጅታዊ አቅምና ልምድ የማካበት መብት እንዳላቸው አውቀው እንዲነሳሱ ጥሪ ለማድረግ እወዳለሁ ። በተለይ የገናናው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ወራሾች የሆኑ የሁሉም ብሄረሰቦች ተማሪዎች፣ የዘረኞች መሳሪያ እየሆነ ያለውን የብሄረሰብ ተማሪ ማህበራት ተንኮልና ድቀት ተሻግረው፣ እንደ አንድ ዜጋ እንዲቆሙና እንዲደራጁ ጥሪ አደርጋለሁ ።

**አባቶቼ፣ እናቶቼ፣ ወንድሞቼ፣ እህቶቼ!**

ይህን ብካይ ዘረኛና አምባገነን ስርአት እንዴት እንደምንጥለው ብቻ ሳይሆን ከአምባገነንነትና ዘረኝነት ባሻገር መፍጠር ስለምንሻት መፃኢቱ ኢትዮጵያ አምርረን መነጋገር መቻል አለብን ። ባለፉት 40 አመታት ሁለት የለውጥና ተሃድሶ ዕድል ገጥሞን፣ ሁለቱንም ጊዜ በብቃት የመጠቀም አቅምና ችሎታ አንሶን፣ በመጀመሪያ ለአምባገነን ወታደሮች፣ ቀጥሎ ለአምባገነን ዘረኞች እድላችንን አሳልፈን ለመስጠት ተገደናል። በዚህም ግራ የመጋባትና፣ በራስ ያለመተማመን፣ የሃገራችንን ታሪካዊ ቀጣይነት የመጠራጠርና፣ የተስፋ ስንቃችንን በማጅራት መቺዎች የመቀማት አደጋ አጋጥሞናል። በራሳችንም ሆነ በሃገራችን ላይ የምንፈፅመው ታላቁ በደል፣ ምርጫ የለንም ብለን እጃችንን አጥፈን፣ የዘረኞችን በደል ለመሸከም ትከሻችንን ያመቻቸን እንደሆነ ነው ።

***ወገኖቼ ሆይ!***

በአዲስ አመት ማዕዳችን ዙሪያ ስንሰበሰብ፣ ለዘረኞች ላለመንበርከክና፣ ህይወታችንን የመለወጥ አቅም በእጃችን እንዳለ አምነን፣ ለልጆቻችን ከተረከብናት የተሻለች ኢትዮጵያን ትተን ለማንቀላፋት፣ ፈጣሪያችን ብርታቱን እንዲሰጠን እንፀልይ። አጥብቀን ከሻነው፣ ከህልም ገነታችን እንደንደርስ የታወቀ ነው ። የምንፈፅመውም ትልቅ ሃጢአት ቢኖር፣ ከማለም ተቆጥበን፣ መፃኢቱን ኢትዮጵያ፣ በዐይነ ህሊናችን ማየት የተሳነን ቀን ነው ። የተሻለ ማድረግ እንችላለን ። እንደ ገብረዬ "ካልተሳካልኝ ይልቅ፣ ያልሞከርኩት ነው የሚቆጨኝ" ብለን፣ ወዳለፈው ውድቀታችን ማተኮር ሳይሆን፣ በህሊናችን ሃይል ተሰበን ልናዋልዳት ስለምንጨነቅላት የኢትዮጵያችን ተስፋ ከማለም እንዳንቆጠብ፤ ሕልማችንን እውን ለማድረግ ደግሞ በተግባር ማድረግ ያለብንን ሁሉ እንድናደርግ አደራ እላችሁዋለሁ። በአዲስ አመት ከዚህ የበለጠ አደራ መጠየቅም አይቻልም ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

**ውድቀት ረግጠው ሊገዙን ለሚፈልጉ ዘረኞች!**